# በCOVID-19 ተጽኖ ለደረሰባቸው ነዋሪዎች የኪራይ ዕርዳታ ፕሮግራሞች

የኪራይ ዕርዳታ እያስፈለገዎት ነው? የመኖሪያ ቤት እና ማህበረሰባዊ ልማት መምሪያ (Department of Housing and Community Development, DHCD) በኮሮናቫይረስ (COVID-19) የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ ተጽኖ የደረሰባቸው ዝቅተኛ-ገቢ ያላቸው የዲስትሪክት ነዋሪዎችን መርዳት የሚችል የኪራይ ዕርዳታ ፕሮግራሞች አሉት።

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ስለ COVID-19 የመኖሪያ ቤት ዕርዳታ ፕሮግራም (COVID-19 Housing Assistance Program, CHAP) እና ተከራይ ላይ የተመሰረተ የኪራይ ዕርዳታ (Tenant Based Rental Assistance, TBRA) ፕሮግራም ዝርዝር መረጃን ያቀርባል። ስለ ዲስትሪክቱ የኪራይ ዕርዳታ እና የመኖሪያ ቤት መረጋጋት ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ በ coronavirus.dc.gov ይገኛል።

## COVID-19 የመኖሪያ ቤት ዕርዳታ ፕሮግራም

**ብቁነት፥**
- የዲስትሪክት ነዋሪ መሆን አለበት
- የኪራይ ክፍያ ጥፋትን ማሳየት አለበት
- እስከ የካቲት 29, 2020 ተከራይቶ ያለው መሆን አለበት
- በቤተሰብ መጠን መሰረት የአማካይ ቤተሰብ ገቢ (Median Family Income, MFI) 80% በላይ የማያገኝ
- በCOVID-19 የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት የሥራ ዕድል በመጥፋቱ የገቢ ቅናሽን ማሳየት አለበት።

**የሚያስፈልጉ ሰነዶች**
- የገቢ ማረጋገጫ (የክፍያ መጠየቂያ፣ W2)
- የተመዘገበ የገቢ መጥፋት ወይም የወጪ መጨመር ማረጋገጫ (ያልተጠበቁ የህክምና ሂሳቦች ወይም ወጪዎች)

**የገንዘብ ዕርዳታ፥**
- እስከ ሦስት ወራት ያለፈው የሚከፈለው ኪራይ ወይም $4,250 (ከዚህ በታች ያለው ሁሉ) ከሚያዝያ 2020 ጀምሮ።

**እንዴት ማመልከት ይቻላል፥**
ይህንን ድረገፅ አድራሻ ይጎብኙ፥ **https://bit.ly/RPPHelp**

**ተጨማሪ መረጃ እና ዕርዳታ፥**
ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ ያሉትን ያግኙ፥
- ታላቋ ዋሽንግተን የከተማ ሊግ (202) 552-2898
- የመኖሪያ ቤት የምክር አገልግሎቶች (202) 667-7713
- የተባበሩ የእቅድ ማዉጣት ድርጅት (202) 231-7910

## ተከራይ ላይ የተመሰረት የኪራይ ዕርዳታ ፕሮግራም

**ብቁነት፥**
- የዲስትሪክት ነዋሪ መሆን አለበት
- የኪራይ ክፍያ ጥፋትን ማሳየት አለበት
- እስከ የካቲት 29, 2020 ተከራይቶ ያለው መሆን አለበት
- ኪራይ ላይ ጥፋተኛ እንደሆኑ ወይም መክፈል እንዳልቻሉ ማሳየት አለባቸው
- በቤተሰብ መጠን መሰረት የአማካይ ቤተሰብ ገቢ (MFI) 60% በላይ የማያገኙ

**የሚያስፈልጉ ሰነዶች**
- ከመጋቢት 13, 2020 በፊት የሁለት ወራት የባንክ አካውንት መረጃ
- ከመጋቢት 13, 2020 በፊት የሁለት ወራት ሁሉም የተገኙ የደመወዝ ገቢ ሰነዶች
- ነዋሪው 18 ዓመት ወይም የሚበልጥ እና የሙሉ-ጊዜ ተማሪ ከሆነ፣ ያሁኑ የምዝገባ ማረጋገጫ ያስፈልጋል
- የደሞዝ ሰነዶች በሌሉበት ጊዜ፣ እባክዎ ሁሉንም ገቢ የሚያካትት መግለጫን፣ የትኛዉም የሥራ-አጥነት ወይም በCOVID-19 ወረርሺኝ ምክንያት የተወሰዱ የድንገተኛ ሁኔታ ጥቅማጥቅሞችን ጨምሮ።

**የገንዘብ ዕርዳታ፥**
- ዕርዳታው በተከራይ ገቢ እና ለክፍሉ ያሉ የአልጋ ክፍሎች ላይ የሚመሰረት ነው።

**እንዴት ማመልከት ይቻላል፥**
ይህንን ድረገፅ አድራሻ ይጎብኙ፥ **https://bit.ly/RPPHelp**

**ተጨማሪ መረጃ እና ዕርዳታ፥**
ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ ያሉትን ያግኙ፥
- የመኖሪያ ቤት የምክር አገልግሎቶች (202) 667-7713
- የላቲኖ ኢኮኖሚያዊ ልማት ማዕከል (202) 588-5102 ወይም (202) 540-7401

## CHAP/TBRA ወርሃዊ ገቢ ገደቦች

| የገቢ ገደብ | 1 ሰው | 2 ሰው | 3 ሰው | 4 ሰው | 5 ሰው | 6 ሰው | 7 ሰው | 8 ሰው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የMFI 30%* | $2,208.33 | $2,520.83 | $2,837.50 | $3,150.00 | $3,404.17 | $3,654.17 | $3,908.33 | $4,158.33 |
| የMFI 50%* | $3,675.00 | $4,200.00 | $4,725.00 | $5,250.00 | $5,670.83 | $6,091.67 | $6,512.50 | $6,933.33 |
| የMFI 60%* | $4,410.00 | $5,040.00 | $5,670.00 | $6,300.00 | $6,805.00 | $7,310.00 | $7,815.00 | $8,320.00 |
| የMFI 80%* | $4,645.83 | $5,308.33 | $5,970.83 | $6,633.33 | $7,166.67 | $7,695.83 | $8,229.17 | $8,758.33 |

*እንዲሁም እንደ አካባቢያዊ አማካይ ገቢ(AMI) ይጠቀሳል
እዚህ የቀረቡ የፕሮግራም ገደቦች ለማሳያ ዓላማዎች ናቸው። የፕሮግራም ገደቦች በጊዜ ሂደት እና እንደ ገቢ መሰብሰቢያ ምንጭ እና በማመልከቻ-ልዩነት ሁኔታዎች ሊለያይ ይችሉ ይሆናል

DHCD.DC.GOV

DERT District Economic Recovery Team

dhcd Department of Housing and Community Development BUILDING ENDURING COMMUNITIES

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR